የወ/መ/ቁጥር 131076

የልደታ ምድብ 2 ኛ ወንጀል ችሎት

ሰኔ 28 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፣ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፣ 1 ኛ አቶ ተክለማርያም ፈታ ኑርጋ - ቀረበ

2 ኛ ወ/ሪት ገነት ሽኩር ለማ - ቀረበች

3 ኛ አቶ ሰይፈስላሴ ፈታ ኑርጋ - ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ሐምሌ 06 ቀን 2001 ዓ.ም አሻሽሌ ፅፎ ባቀረበው የወንጀል ክስ አቤቱታ ሁለት ክሶችን ያቀረበ ሲሆን በመጀመሪያው ክስ ሦስቱም ተከሳሾች በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ) እና 689 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ለወንጀል ሥራ ግብረአበር በመሆን ሰኔ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ሲሆን በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 ልዩ ቦታው መካኒሳ አትክልት አምራቾች አካባቢ ከሚገኘው የግል ተበዳይ አቶ ግርማ ተክሉ መኖሪያ ቤት የግቢውን አጥር አፍርሰው ወደ መኖሪያ ግቢው በመግባት በግቢ የሚገኘውን የግራዋ ተክል በመጥረቢያ መቁረጣቸው በፈፀሙት በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሰዋል፤ በሁለተኛው ክስ አንደኛ ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ፍርሀትና ድንጋጤ በሚፈጥር ሁኔታ በአንደኛው ክስ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ የግል ተበዳይ አቶ ግርማ ተክሉ በእጁ በያዘው መጥረቢያ አንገትህን በዚህ መጥረቢያ ነው የምቆርጠው ብሎ በመዛቱ በፈፀመው የዛቻና ማስፈራራት ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሾች ደርሷቸውና ተነቦላቸው ከተረዱት በኋላ ክሱን ሳይቃወሙ፤ ድርጊቱን አልፈፀምንም፤ ጥፋተኞችም አይደለንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ዐ/ሕግ የግል ተበዳይን ጨምሮ አራት ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የተሰሙት ምስክሮችም ተከሳሾች በክሱ ላይ የተመለከተውን ድርጊት መፈፀማቸውን በማስረዳታቸው ሁሉም ተከሳሾች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 689 ስር፤ አንደኛ ተከሳሽ ደግሞ በተጨማሪ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 ስር እንዲከላከል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዘዋል።

ተከሳሾችም እንከላከላለን ብለው ሁለት የመከላከያ ምስክሮን አቅርበው ያሰሙ ሲሆን በመከላከያ ጭብጥነትም በወቅቱ በእኛና በግል ተበዳይ መካከል የመሰኖ ቦይ ያለ ሲሆን፤ ይህ ቦይ መፅዳት ስላለበትና እኛን የሚያስቀጣ ስለሆነ፤ አንደኛ ተከሳሽ ቦዩን እያፀዳሁ ሳለ የግል ተበዳዩ መጣና ውጣ ሲለኝ፤ እኔ ደግሞ ለምንድነው

የምወጣውን እያፀዳሁ ነው ስለው በግቢው የነበሩ ሰዎች መጥተው አገላገሉን፤ ወዲያው ዝናብም መጣና ተለያየን፤ ሁለተኛ ተከሳሽ በወቅት ግቢ ውስጥ ልብስ በማጠብ ላይ ነው የነበርኩት፤ ቦዩንም አላፀዳሁም፤ ሦስተኛ ተከሳሽ ደግሞ ከእነጭራሹ በቦታው አልነበርኩም፤ የነበርኩትም ቤተክርስቲያን ነው በማለት ያስመዝገቡ ሲሆን የመከላከያ ምስክሮቹም ቀርበው በእምነታቸው መሰረት መጎላ ፈፅመው የመሰከሩ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪ ፍ/ቤቱ ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ያስፈልጋል በማለት ከክፍሉ የቀበሌ አስተዳደር በደንብ አስከባሪዎች አማካኝነት በቦታው ጉዳት ደርሶበታል፤ ከእነጭራሹ ተቆርጧል የተባለውን ትልቅ የግራዋ ዛፍ በተመለከተ መኖርና አለመኖሩ ተጣርቶ እንዲቀርብ ብሎ በዚሁ መሰረት ተጣርቶ ቀርቧል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሾች ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ አስተባብለዋል ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን በተከሳሾች በኩል የቀረቡት የመከላከያ ምስክሮች በወቅቱ በቦታው እንደነበሩ ገልፀው፤ በግል ተበዳይና በአንደኛ ተከሳሽ መካከል ንግግርና የመጣለት ነገር የተፈፀመ መሆኑን ገልፀው፤ ነገር ግን በእነሱና በቦታው በነበሩ ሰዎች አማካኝነት ያገላገሏቸው መሆኑን አስረድተዋል። በወቅቱም ሁለተኛ ተከሳሽ ግቢዋ ውስጥ ልብስ እያጠበች እንደነበር፤ ሦስተኛ ተከሳሽ ደግሞ ከእነአካቴው በቦታው ያልነበረ መሆኑን፤ በወቅቱም አንደኛ ተከሳሽ የቆረጠው የግራዋ ዛፍ አለመኖሩን፤ ምክንያቱም ዛፉ በቦታው ስለነበረ ነው ብለውም አስረድተዋል። ከዚህ ሌላ በተከሳሾች ተቆረጠ የተባለው ትልቅ የግራዋ ዛፍ በአሁኑ ወቅትም ያለ መሆኑን የክፍሉ የቀበሌ አስተዳደር አጣርቶ ለፍ/ቤቱ መልስ ሰጥቷል። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አንደኛውን ክስ በተመለከተ ተከሳሾች በግል ተበዳይ ንብረት ላይ ጉዳት አድርሰዋል የሚለውን ክስና ማስረጃ በተመለከተ ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ ያስተባበሉ ስለሆነ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 689 ተጠቅሶ ከቀረበባቸው ክስ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(2) መሰረት በነፃ ተሰናብተዋል።

ሁለተኛውን ክስ በተመለከተ ግን የተከሳሽ የመከላከያ ምስክሮች በወቅቱ በግል ተበዳይ እና በአንደኛ ተከሳሽ መካከል ንግግርና የቃላት መለዋወጥ ነበር፤ ነገር ግን ሰዎች ደርሰው ገላገሏቸው በማለት ያስረዱ ስለሆነ፤ ይህ ደግሞ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበውንና አንደኛ ተከሳሽ የዛቻ የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል የተባለውን የሚያጠናክር በመሆኑ፤ እነዚህ የመከላከያ ምስክሮችም አንደኛ ተከሳሽ ይህን የዛቻ የወንጀል ድርጊት አልፈፀመም በማለት ያላስተባበሉለት ስለሆነ አንደኛ ተከሳሽ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 ስር ጥፋተኛ ነው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ተወስኗል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ አንደኛ ተከሳሽ የዛቻ ወንጀሉን የፈፀመው መጥረቢያ ይዞ ስለሆነ፤ ፍ/ቤቱ

የወንጀል ደረጃውን ሲያወጣ ከባድ በማለት መድቦ የሚያርምና

የሚያስተምር ቅጣት እንዲወሰን በማለት አመለከቱ።

<u>አንደኛ ተከሳሽ</u>፡ የትምህርት ደረጃዬ ፤ ዕድሜዬ ፤ ትዳርና ልጅ የለኝም፤

የምተዳደረው በንግድ ሥራ ሲሆን፤ የወር ገቢዬ ብር

300.00(ሦስት መቶ ብር) ነው በማለት አመለከተ።

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

አንደኛ ተከሳሽ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 580/የዛቻ ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት አንደኛ ተከሳሽ ወንጀሉን የፈፀመው ገዳይ መሳሪያ የሆነውን መጥረቢያ ይዞ በመሆኑ፤ የወንጀል ደረጃው መካከለኛ ነው ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት እርከን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 580 ለወንጀሉ የተቀመጠው መነሻና መድረሻ ከአስር ቀን እስከ አንድ መቶ ሰማንያ ቀን ቀላል እስራት የቅጣት እርዝመት ለአራት ተከፍሎ ስሌቱን በመስራት የተገኘው ውጤት ከባድ ደረጃ የሚለው የሚወድቀው ከሃምሳ ሁለት ቀን እስከ ዘጠና አምስት ቀን ባለው መካከል ስለሆነ በመመሪያው አንቀፅ 13(7) መሰረት ሰባ አምስት ቀን መነሻ ቅጣት ተብሎ ተወስኗል።

ይህ በፍ/ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት በአባሪ አንድ እርከን 2 ላይ የሚታይ ሲሆን ፍቃደ ስልጣኑም/range/ ከአስር ቀን እስከ ሦስት ወር እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን በፍ/ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት ሁለት ወር እስራት ነው።

ከዚህ በመነሳት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84 እና 85 መሰረት በማስረጃ የተደገፈ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ስላላቀረበ ከላይ የተመለከተው እርከን ከፍ አልተደረገም።

ተከሳሽም የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርብ ተጠይቆ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 ላይ በተገለፁት መሰረት አላቀረበም። ስለሆነም ፍ/ቤቱ ከላይ የተመለከተውን የቅጣት እርከን ዝቅ አላደረገውም።

ስለሆነም ከላይ እንደተገለፀው ቅጣቱ በአባሪ አንድ እርከን 2 ላይ በተመለከተው ፍቅድ ስልጣን/range/ ከአስር ቀን እስከ ሦስት ወር እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ባለመኖሩ በሁለት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ከሰኔ 28 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ በማሰብ
የተወሰነው የእስራት ቅጣት እንዲያስፈፅም ታዟል።

2 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

3 ኛ. በዚህ መዝገብ የተገባ የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል።

4 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።